ሕገ ቤተ ክርስቲያን

አጭር ርእስ

- ይህ ሕግ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የ1991 ዓ.ም ሕገ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ትርጓሜ

- የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ሕግ ውስጥ፣
- “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን” ማለት ክርስቶስን በተዋሕዶ አንድ አካል፣ እና አንድ ባሕርይ፣ ብላ የምታምን ሐዋርያዊት፣ ጥንታዊት፣ ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ናት።
- “ቅዱስ ሲኖዶስ” ማለት ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት የሚያደርጉት ዐቢይ ጉባኤ ነው።
- “ፓትርያርክ” ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ አበው አበ ብዙኀን ማለት ነው።
- “ሊቀ ጳጳስ” ማለት በኤጲስ ቆጶስነት ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ ሊቀ ጳጳስ ተብሎ የሚሠየም የቤተ ክርስቲያን አባት ነው።

- “ኤጲስ ቆጶስ” ማለት በድንግልና መንኩሶ ቤተ ክርስቲያንን በዲቁናና በቅስና እንዲሁም በቁምስና ሲያገለግል ከቆየ በኋላ የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ የተቀበለ የቤተክርስቲያን ጠባቂ ወይም ኖላዊ ማለት ነው።

“ቋሚ ሲኖዶስ” ማለት

ሀ/ ቅዱስ ፓትርያርክ

ለ/ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ

ሐ/ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ

መ/ ከሲኖዶስ አባላት መካከል ዐራት ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ኤጲስ ቆጶሳት በአባልነት የሚገኙበት ጉባኤ ነው።

- “የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ” ማለት የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ነው።
- “ጠቅላይ ጽ/ቤት” ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ (ቤተ ክህነት) ጽ/ቤት ነው።
- “ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ” ማለት በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ተመርጦ በፓትርያርኩ የተሠየመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ (ቤተ ክህነት) ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ነው።

- “አስተዳደር” ማለት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከአጥቢያ እስከ ሀገረ ስብከት ከዚያም እስከ ጠቅላይ (ቤተ ክህነት) ጽ/ቤት ያለውንና የድርጅቶችን አመራር የሚያጠቃልል የአስተዳደር ሥራ ነው።
- “የአስተዳደር ጉባኤ” ማለት በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የሚመራ የመምሪያና የድርጅት ሓላፊዎች የሚገኙበት ስበሰባ ነው።
- “መምሪያ” ማለት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሚገኝ ዐቢይ የሥራ ዘርፍ ነው።
- “ሀገረ ስብከት” ማለት የሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና ነው።
- “መሥሪያ ቤት” ማለት ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት እስከ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በየደረጃው የተቋቋሙት የድርጅቶች ጽ/ቤት ነው።
- “ሠራተኛ” ማለት በቤተ ክርስቲያኒቱ መ/ቤቶች በቋሚነት ወይም በክነትራት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ሰውነት

- ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አምላክ የመሠረታት በምድር ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት ስለሆነች ራሷን የመምራትና የማስተዳደር መብት አላት፣
- በሀገሪቱ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 398 እና 399 በሐይማኖታዊ መሠረት

ሀ/ በመሥሪያ ቤቶቿ አመካኝነት በአስተዳደር ሕጐች የተፈቀዱትን መብቶች ሁሉ ልታገኝና ልትሠራባቸው

ለ/ ውል ለመዋዋል፣ ለመክሰስና ለመከሰስ ባለንብረት ለመሆን ለመግዛት፣ ለመሸጥና ውርስ ለመቀበል ትችላለች።

- ቤተ ክርስቲያኒቱ በምታስተዳድራቸው ካህናትና ምእመናን ላይ ባላት የዳኝነት ሥልጣን መሠረት፣

ሀ/ በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ውስጥ ለሚፈጸሙ የሥራ ጉድለቶች በቤተክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዐት መሠረት የመቆጣጠር፣ የመቅጣት፣ የማረም፣ ከሥራ የማስወገድ በጡረታ የማግለል ወዘተ.... መብት አላት።

ለ/ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዳኝነት እንደክሱ አቀራረብ እየተመዘነ የሚታየው፣

1. በዲሲፕሊን ጉባኤ /በሥነ ሥርዐት ጉባኤ/
2. በመንፈሳዊ ፍ/ቤት
3. በአስተዳደር ጉባኤ
4. በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ነው። በቅ/ሲኖዶስ የሚወሰኑ ውሳኔዎችም የመጨረሻ ይሆናሉ።

ሐ/ የእያንዳንዱም የዳኝነት ሥልጣን ከቤተ ክርስቲያኒቱ በሚወጡ ሕጐችና ደንቦች ይወሰናል።

መ/ ካህናት፣ ኤጲስ ቆጶሳትና ሊቃነ ጳጳሳት መንፈሳዊ ሥራቸውን (አገልግሎታቸውን) በሚመለከት ጉዳይ ሲከሰሱ በቤተ ክርስቲያን ሕግና የዳኝነት ሥርዓት ይታያል እንጂ በሥጋዊ ዳኝነት አይከሰሱም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሥልጣን መዋቅር

1. ቅዱስ ሲኖዶስ
2. ፓትርያርክ
3. ቋሚ ሲኖዶስ
4. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት
5. የሀገረ ስብከት ክህነት
6. የወረዳ ቤተ ክህነት
7. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ

የቅዱስ ሲኖዶስ ልዕልና /የበላይነት/

- በመንፈስ ቅዱስ የሚመራው ቅ/ሲኖዶስ የመንበረ ሐዋርያት ወራሽ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛ ሥልጣን ባለቤት ነው።
- ከማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣን መዋቅር ሁሉ የበላይ አካል ቅድስ ሲኖዶስ ስለሆነ ሕጐችን ፣ ልዩ ልዩ ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣትና የዳኝነት ሥልጣን አለው።

የቅዱስ ሲኖዶስ ዓላማ

1. ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ አገልግሎቷም የተሟላ እንዲሆን ለማድረግ፣
2. ሃይማኖትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንዳይፋለስ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ፣
3. ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለመጠበቅና ለማስፋፋት፣
4. ስብከተ ወንጌልን ለማስፋፋትና ለማጠናከር፣
5. ወጣቶች ከአበው የተቀበሉትን ሃይማኖትና ሥርዐት ጠብቀው በትምህርትና በሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ሰንበት ት/ቤትን ለማጠናከርና ለማስፋፋት፣
6. የሰው ዘር ሁሉ ከርኅብ፣ ከእርዛት፣ ከበሽታና ከድንቁርና ተላቆ በሰላምና በአንድነት በመተሳሰብና በመረዳዳት በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲኖር ማስተማርና መጸለይ፣

የቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣንና ተግባር

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።
- ቅዱስ ሲኖዶስ ቤተ ክርስቲያን በበላይነት ይመራል፣ ይጠብቃል።

- የቤተ ክርስቲያኒቱን አጠቃላይ የምጣኔ ሀብትና የሙዓለ ንዋይ መመሪያዎችን /ፖሊሲዎችን/ ይወስናል።
- ዓመትዊውን በጀት ያጸድቃል ተግባራዊነቱንም ይቆጣጠራል።
- የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደራዊ መዋቅር እንዲሁም የጽሕፈት ቤቶችን ደረጃና ተጠሪነት ያደርጋል።
- የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደርና አገልግሎት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት እንዲመራ ያደርጋል።
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት በአገር ውስጥና በውጭ አገር እንዲስፋፋ ያደርጋል። ትምህርት ቤቶችንም ያቋቁማል።
- የክርስቶስን ወንጌል መንግሥትና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ያስተምራል ያስፋፋል።
- በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር አዲስ የሀገረ ስብከት ጽሕፈት ቤትና መንበረ ጵጵስና እንደ አስፈላጊነቱ ያቋቁማል።
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን ግንኙነት ያስፋፋል ያጠነክራል።
- ማንኛውም ሰው ቤተ ክርስቲያኒቱን ወክሎ ለሥራም ሆነ ለጉብኝት ወደ ውጭ አገር በሚላክበት ጊዜ ቅዱስ ሲኖዶስ እየፈቀደ ነው።

- ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሾሙ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ቅዱስ ሲኖዶስ በምልዓተ ጉባኤ እየወሰነ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ መሠረት እንዲመረጡና እንዲሾሙ ያደርጋል። እንዲሁም ሊቃነ ጳጳሳትንና ኤጲስ ቆጶሳትን በየሀገረ ስብከቱና በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ይመድባል በበቂ ምክንያት ያዘዋውራል።
- በቋሚ ሲኖዶስ የሚያገለግሉ ጳጳሳትን በየሦስት ወሩ እየመደበ እንዲሠሩ ያደርጋል።
- በኢትየጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚመደቡትን

  ሀ/ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ፈሐፊ

  ለ/ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ

  ሐ/ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቱ ም/ሥራ አስኪያጅ

መ/ የልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር

ሠ/ የውጭ ጉዳይ መምሪያ ሓላፊ

ረ/ የልዩ ልዩ ሥራ ዘርፎች ቦርድ አባላት እየመረጠ እንዲሾሙ ያደርጋል።

- ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው በሚያደርጋቸው ስብሰባዎች የሚቀርቡትን አጀንዳዎች ያጸድቃል እንደአስፈላጊነቱም ያሻሽላል።
- ቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል። ለጥፋተኞችና ለበደለኞችም ምሕረትና ይቅርታ የመስጠት ሥልጣን የቅዱስ ሲኖዶስ ነው።
- በዚህ ሕግ ባልተካተቱ በማናቸውም በቤተ ክርስቲያኒቱ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ቅዱስ ሲኖዶስ የመወሰን ሥልጣን አለው።

የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት

1. በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ሆነው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አኅጉረ ስበከትና በልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የተሾሙ ሁሉ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ናቸው።
2. ከፓትርያርኩ ጀምሮ እያንዳንዱ ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስና ኤጲስ ቆጶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው።
3. የቅዱስ ሲኖዶስ አባልነት ዕድሜ ልክ ይሆናል።
4. አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚያፋልስ ሆኖ ከተገኘ ከአባልነቱ ይሰረዛል።
5. ይህም የሚሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ነው።
6. በሃይማኖታም ሆነ በቀኖና ቤተ ክርስቲያና የተሰሰ የሲኖዶስ አባል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ቀርቦ ራሱን የመከላከል መብቱ የተጠበቀ ነው።
7. አንድ የሲኖዶስ አባል ስለራሱ ጉዳይ በሚታይበት ስብሰባ ላይ በአባልነት መገኘት አይችልም።

የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ

- የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በፓትርያርኩ ሰብሳቢነት ይመራል። ፓትርያርኩ በልዩ ልዩ ምክንያት ጉባኤውን መምራት ባይችል ከአባላቱ መካከል እሱ የሹመት ቅድምና ያለውን አባት በመወከል ስበሰባው ሊመራ ይችላል።
- ከዚህ በታች ከተመዘገቡት በሦስት ምክንያቶች ካልሆነ በቀር ፓትርያርኩ ርእሰ መንበር ያልሆነበት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ሊካሔድ አይችልም።

ሀ/ ፓትርያርኩ በዕርግናና በጤና ጉድለት ምክንያት ጉባኤውን የሚመራ አባት መወከል ካልቻለ፣

ለ/ የቤተ ክርስቲያንን እምነትና ቀኖና በተመለከተ የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ እንዲደረግ የሲኖዶሱ አባላት ሲጠይቁት ፈቃደኛ ሳይሆን ከቀረ፣

ሐ/ ስብሰባው ፓትርያርኩን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ በፍትሐ መንፈሳዊ መሠረት ይፈጽማል።

- ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፓትርያርኩ ጉባኤውን መምራት ካልቻለ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በተመረጠ የሹመት ቅድመና በአለው አንድ አባት ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል።

የቅዱስ ሲኖዶስ የስብሰባ ሥርዐት

ሀ/ የመጀመሪያው ጉባኤ በየዓመቱ ጥቅምት 12 ቀን

ለ/ የሁለተኛው ጉባኤ ትንሣኤ በዋለ በሃያ አምስተኛው ቀን /በርክበ ክህናት/ የሚካሔደው ነው። አስቸኳይና ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥም

ሀ/ ቅዱስ ፓትርያርኩ ወይም ቋሚ ሲኖዶስ በሚያደርጉት ጥሪ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሊካሔድ ይችላል።

ለ/ ከጠቅላላው አባላት ከሦስት ሁለት እጅ የሚሆኑ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ምልዓተ ጉባኤ እንዲደረግ በጠየቁ ጊዜም ጥሪ ሊደረግና ስብሰባው ሊካሄድ ይችላል።

- የቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓት ጉባኤ የሚባለው ከዓቅም በላይ የሆነ እክል ካላጋጠመ በቀር መላው አባላት የተገኙበት ጉባኤ ሲሆን ነው።

በሕመምና በልዩ ልዩ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት አንዳንድ አባላት ባይገኙ፣

ሀ/ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት ጉዳይ ከጠቅላላው አባላት ከዐራት ሦስት እጅ የተገኙ ከሆነ፣

ለ/ አስተዳደርን በሚመለከት ጉዳይ ከጠቅላላው አባላት ከሦስት ሁለት እጅ የተገኙ ከሆነ ነው። ቅዱስ ሲኖዶስ በማናቸውም ስብሰባ ላይ ውሣኔዎችን ሲያሳልፍ፣

ሀ/ አስተዳደርን የሚመለከት ጉዳይ ከሆነ ከተገሁነት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ በነ ዱምፅ የተደገፈው ሐሳብ ያልፋል።

ለ/ አንድን ጉዳይ ለመወሰን የአባላቱ ድምፅ እኩል በኩል ከሆነ ቅዱስ ፓትርያርኩ ያለበት ያልፋል።

ሐ/ ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከት ከሆነ በሙሉ ድምፅ ያልፋል።

የቋሚ ሲኖዶስ አባላትና ስብሰባ

1. ቋሚ ሲኖዶስ በየሦስት ወሩ አባላቱ እየተተኩ ሥራው በቋሚነት የሚሠራበት፣ ሕግን የመተርጐምና የማስፈጸም መብት ያለው አካል ነው።
2. የቋሚ ሲኖዶስ ሰብሳቢ ፓትርያርክ ነው፤ ፓትርያርኩ በማይኖርበት ጊዜ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ተወክሎ ሰብሳቢ ይሆናል። አባላቱም በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ የተመረጡ አራት ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ኤጲስ ቆጶሳት ይሆናሉ።
3. የቋሚ ሲኖዶስ ስብሰባ በየዕለቱ ይሆናል።
4. ቋሚ ሲኖዶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው።

የቋሚ ሲኖዶስ ሥልጣንና ተግባር

1. በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ እየተወሰኑ የሚተላለፉ መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ጉዳዮች ተግባራዊ መሆናቸውን በየዕለቱ ይከታተላል።
2. የቅዱስ ሲኖዶስን ምልዓተ ጉባኤ የማያስፈልጉ አስተዳደር ነክ በሆነ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ጀመስናል።
3. ከየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት የሚቀርበው የሥራ ሪፖርት ተቀነባብሮ ለቅዱስ ሲኖዶስ እንዲቀርብ ያደርጋል።
4. ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው በሚያደርገው ጉባኤ የሚነጋገርባቸውን አጀንዳዎች ያዘጋጃል።
5. አስቸኳይና ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋይም የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ እንዲደረግ ይወስናል።
6. ዓመታዊ በጀት ተጠንቶና ተዘጋጅቶ በዚህ ሕግ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት እንዲጸድቅ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ያቀርባል።
7. ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያኒቱ ገቢና ወጭ በበጀት መሠረት መሠራቱን ይቆጣጠራል።

ስለ ቅዱስ ፓትርያርክ ምርጫ

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ቀኖና በሚፈቅደው መሠረት ተመርጦ ይሾማል።
- ቅዱስ ሲኖዶስ ስለፓትርያርክ ምርጫ በሚወስነው ቁጥር መሠረት አስመራጭ ኮሚቴ ይቋቋማል፣
- ለፓትርያርክነት የሚመረጡት እጩዎች ከሊቃነ ጳጳሳትና ከኤጲስ ቆጶሳት መካከል ሲሆን ብዛታቸው ከሦስት ያላነሱ ከአምስት ያልበለጡ ይሆናል።
- አስመራጭ ኮሚቴው እጩዎችን ጠቁሞ ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዐት መሠረት ምርጫው እንዲካሔድ ይደርጋል።

- መራጮች የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት በሙሉ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የየመምሪያና ድርጅት ሓላፊዎች፣ የጥንታውያን ገዳማት አበምኔቶች፣ የአድባራት አስተዳዳሪዎች ከየሀገረ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤያት በዕድሜ ከ 30 ያላነሱ የካህናትና የምእመናን ተወካዮች እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ 22 እስከ 30 ዓመት የሆኑ የሰንበት ት/ቤት ተወካዮች ሲሆኑ በጠቅላላው በሰበካ ጉባኤው የሚወክሉት ከአንድ ሀገረ ስብከት ዐሥራ ሁለት ሆነው በሥጋ ወደሙ የተወሰኑ በሕገ ቤተ ክርስቲያን የጸኑ መሆን አለባቸው።
- የምርጫው አፈጻጸም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።
- የተመረጠው ፓትርያርክ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትንና ቀኖናዋን ሊጠብቅና አድልዎ በሌለው መልኩ ቤተክርስቲያኒቱን ሊያስተዳድር ቃለ መሐላ ይፈጽማል።
- ከዚህ በላይ የተደገገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፓትርያርክ ምርጫ ቅዱስ ሲኖዶስ ደንብ ያወጣል።

የፓትርያርኩ የማዕረግ ስምና መንበር

- ፓትርያርኩ ከተሾመበት ቀን ጀምሮ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ እገሌ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ይባላል፤ ስሙም በመላዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በጸሎት ይጠራል።
- ፓትርያርኩ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ለሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን መንፈሳዊ አባት ነው።
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ መንበር በአዲስ አበባ ከተማ በቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ነው።

የፓትርያርኩ ሥልጣንና ተግባር

- ፓትርያርኩ በተሰጠው ሓላፊነት መሠረት ሃይማኖትንና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቃል ያስጠብቃል።

- ፓትርያርኩ ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጋር ሆኖ ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾማል፣ እንዲሁም ቅዱስ ሲኖዶስ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሲስማማበት ለብፁዓን ጳጳሳት የሊቀ ጵጵስና ማዕረግ ይሰጣል።
- የተመረጡትን የሥራ ሓላፊዎች ይሾማል፣ በቀደምትነት በታሪክ የታወቁትን የታላላቅ ገዳማት አበምኔቶችና የከፍተኛ አድባራት አስተዳዳሪዎች በየሀገረ ስብከቱ ሊቃነ ጳጳሳት እየተመረጡ ሲቀርቡለት የማረግ ስም እየሰጠ ይሾማል።
- ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የመንግሥትን ፈቃድ ማግኘት በሚያስፈልግበት ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ እያስወሰነ በተግባር ላይ ያውላል።
- ቅዱስ ፓትርያርኩ በዐበይት ጉዳዮች ላይ ሁሉ በቅዱስ ሲኖዶስ እያስወሰነ ይሠራል።
- በቅዱስ ሲኖዶስ የወጡ ሕጐች፣ የተላለፉ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ሁሉ በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
- በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወጡትን ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በፊርማው ያስተላልፋል።
- ፓትርያርኩ በውጭ አገር በሚደረግ በማናቸውም ስበሰባ ላይ ለመገኘትና ጉብኝት ለማካሔድ በሚያስፈልግ ጊዜ ስለ ተልእኮው ጉዳይ አስቀድሞ በቅዱስ ሲኖዶስና በቋሚ ሲኖዶስ ያስወስናል።

የፓትርያርኩ ከማዕረግ መውረድ

- ፓትርያርኩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከተሾመ በኋላ የተቀበለውን ሐላፊነት በመዘንጋት።
- ሀ/ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን የሚያፋልስ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቅ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስነቅፍ ተግባር ፈጽሞ ከተገኘ፣
- ሐ/ በቃሉ የማይገኝና በተሾመበት ቀን የፈጸመውን ቃለ መሐላ ያልጠበቀ በአጠቃላይ ታማኝነቱ መንፈሳዊ አባትነቱ በካህናትና በምእመናን ዘንደ ተቀባይነትን ያጣ ሆኖ ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚያስነቅፍ መሆኑ በትክክል ከተረጋገጠ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከሥልጣኑ ይወርዳል፤ በምትኪም ሌላ ፓትርያርክ ተመርጦ ይሾማል።
- ከዚህ በላይ በተደነገገው መሠረት ከሥልጣኑ የተገለለ ፓትርያርክ በቀኖና ተወስኖ በገዳም ይቀመጣል።

- ከሥልጣን የተገለለው ፓትርያርክ በገዳም አልቀመጥም በቀኖናም አልወሰንም በማለት እምቢተኛ ከሆነ ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን አንድነት ይለያል።
- ፓትርያርኩ መንፈሳዊ ሥራውን በማካሔድ ላይ እያለ እሥራትና ግዞት ቢደርስበት ቤተ ክርስቲያኒቱ በቅዱስ ሲኖዶስ ትመራለች እንጂ ሌላ ፓትርያርክ አይሾምም።
- ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሁሉ ፍትሕ መንፈሳዊ በሚያዝዘው መሠረት ይፈጸማል።

ስለ ኤጲስ ቆጶሳት

የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠት ከኤጲስ ቆጶስ ምርጫ የሚፈጸመው፣

- ኤጲስ ቆጶስ እንዲሾም አስፈላጊ መሆኑ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሲታመንበትና ሲወሰን፣
- በሥርዐተ ምንኩስና በድንግልና መንኩሰው ቤተ ክርስቲያንን ከሚያበገለግሉና ለኤጲስ ቆጶስነት ብቁ ከሆኑት ቆሞሳት መካከል በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ዕጩ ሆኖ ሲቀርብ፣
- ለኤጲስ ቆጶስነት ዕጩ ሆኖ የሚቀርበው ቆሞስ ከዚህ የሚከተለውን መመዘኛ የሚያሟላ ሆኖ ሲገኝ ነው።

ሀ/ ቆሞሱ በመነኮሰበት ገዳም ከሦስት ዓመታት ባላነሰ ጊዜ ያገለገለ፣

ለ/ በዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ባይሆንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ ሆኖ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ ያወቀ፣

ሐ/ በትምህርት ሃይማኖት /በነገረ መለኮት/ በቂ ችሎታ ያለውና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን ጠንቅቆ ያወቀ፣

መ/ በግብረ ገብነቱ የተመሰገነ፣

ሠ/ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ፅኑዕ የሆነ፣

ረ/ ሙሉ አካል ያለው ፣ ጤንነቱ የተሟላ፣

ሰ/ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በመፈጸም የአስተዳደር ልምድ ያለው፣

ሸ/ ዕድሜው ከ 45 እስከ 60 ዓመት የሆነው፣

ኤጲስ ቆጶስ በሚመረጥበት ጊዜ በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሰየም አስመራጭ ኮሚቴ ተጠቁሞ የሚቀርብ ይሆናል።

የኤጲስ ቆጶስ ሥልጣንና ተግባር

- ኤጲስ ቆጶስ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስና ለፓትርያርኩ ነው፣ ካህናትንና ምእመናንን የመምራት፣

የማስተማር፣ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የመፈጸምና የማስፈጸም ሙሉ ሥልጣን አለው።

- በሀገረ ስብከት የተሾመ ኤጲስ ቆጶስ ለሊቀ ጳጳስ የተሰጠው ሥልጣንና በተግባር ለኤጲስ ቆጶሱም ይሆናል።
- ኤጲስ ቆጶሱ በተሾመበት ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ካለ ኤጲስ ቆጶሱ ተጠሪነቱ በሀገረ ስብከቱ ላለው ሊቀ ጳጳስና ለቅዱስ ሲኖዶስ ሆኖ ከሊቀ ጳጳሱ ጋር እየተመካከረና መመሪያ እየተቀበለ ይሠራል።

የኤጲስ ቆጶስ ግዴታና ሓላፊነት

- ኤጲስ ቆጶሱ በተሾመበት ሀገረ ስብከት ይኖራል።
- በፓትርያርኩ ፈቃድ ወይም በሥራ ምክንያት ወይም በሕመም ምክንያት ካልሆነ በቀር ከሀገረ ስብከቱ ውጭ ከዐሥራ አምስት ቀን የበለጠ መቆየት አይችልም።
- ሊቀ ጳጳሱ ወይም ኤጲስ ቆጶሱ ሳይፈቀድለት ወይም ሳይጠይቅ በሌላው ሀገረ ስብከት ገብቶ ክህነት መስጠት፣ መዳኘት ፣ አዲስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት መባረክና የመሳሰሉትን ዐበይት ተግባራት መፈጸም አይችልም፤ ይህን አድርጐ ቢገኝ የተጠቀሰው አንቀፍ በሚያዝዘው መሠረት ይፈጸማል።
- ኤጲስ ቆጶሱ በዓመት ሁለት ጊዜ ለሚደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ጉባኤ የሥራ ሪፖርት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ያቀርባል፤ በምልዓተ ጉባኤው ስብሰባ ላይም ይገኛል።

- ያለበቂ ምክንያትና ያለቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የኤጲስ ቆጶስነቱን ማዕረግ በፈቃዱ እንዲተው አይፈቀድለትም።
- ኤጲስ ቆጶሱ በጊዜ ዕረፍቱ የኤጲስ ቆጶስነት ተልእኮውን ሲፈጽም ከኖረበት ሀገረ ስበከት ይቀበራል።

ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ

የዋና ጸሐፊው ምርጫ

- በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በሚሠየም አስመራጭ ኮሚቴ አቅራቢነት ከሲኖዶስ አባላት መካከል ሦስት ተወዳዳሪዎች ቀርበው በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ይመረጣል።
- ለቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊነት የተመረጠው ሊቀ ጳጳስ ፣ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ በቅዱስ ፓትርያርኩ ይሾማል።
- የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ የሲኖዶስ አባልና ጸሐፊ ሆኖ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ይሁንና የዕለት ከዕለት ሥራውን ከቅዱስ ፓትርያርኩ መመሪያ እየተቀበለ ይሠራል።
- የሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ለአንድ የምርጫ ዘመን እንደገና ሊመረጥ ይችላል።
- ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተመረጠው ጸሐፊ የጸሐፊነቱን ሥራ ለመቀጠል የማያስችለው በቂ ምክንያት ባጋጠመ ጊዜ ባይደርም በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ በሌላ ሊተካ ይችላል።

የቅዱስ ሲኖዶስ ጸሐፊ ሥልጣንና ተግባር

- ቅዱስ ሲኖዶስ በየጊዜው በሚያደርገው ጉባኤ ላይ ሁሉ በቋሚ ሲኖዶስ የሚዘጋጀውን ርእሰ ጉዳይ /አጀንዳ/ ለቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ያቀርባል።
- በየጊዜው በሚያደርገው በቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ እየተገኘ ቃለ ጉባኤ ይይዛል።
- ከቅዱስ ሲኖዶስ የሚሰጠውን ውሳኔና ትእዛዝ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያስተልልፋል።
- የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች ሁሉ በተግባር ላይ መዋላቸውን ይከተተላል፣ይቆጣጠራል።
- የሚተላለፈው የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔና ትእዛዝ በሥራ ላይ ካልዋለ ምክንያቱን በመግለጽ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሪፖርት ያቀርባል።
- ጸሐፊው በቅዱስ ሲኖዶስ ያልተወሰነ ጉዳይ ማስተላለፍ አይችልም።
- በጠቅላይ ጽ/ቤት ውስጥ ዋና ጸሐፊው አንድ ጽ/ቤት ይኖረዋል፤ የሲኖዶሱን ማኅተምና ልዩ ልዩ ሰነዶችን ተረክቦ በጥንቃቄ ይይዛል።

የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ

- የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ይመረጣል።
- የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ ችሎታና ሥልጣነ ክህነት ያለው ይሆናል።
- ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ነው።

የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ ተግባር

- የቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ጸሐፊ ከዋና ጸሐፊው መመሪያ እየተቀበለ ለዋና ጸሐፊው ረዳት ሆኖ ይሠራል።
- የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ ነው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት መዋቅር

- ጠቅላይ ጽ/ቤቱ የሥራ አስፈጻሚነትና የአስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ከፈተኛ አካል ነው።
- በቅዱስ ሲኖዶስ የተሠየመ አንድ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅና አንድ ምክትል ሥራ አስክያጅ ይኖሩታል።
- የመምሪያ ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበትና በጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ የሚመራ አንድ አስተዳደር ጉባኤ ይኖረዋል።
- በጠቅላይ ጽ/ቤቱ ሥር ኮሚሽን፣ መምሪያዎች፣ ድርጅቶችና ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ይኖራሉ። እነሱም

ሀ/ መምሪያዎችና የአገልግሎት የሥራ ዘርፎች፣

1. ሊቃውንተ ጉባኤ
2. ስብከተ ወንጌል መምሪያ
3. ትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ
4. መንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ
5. ሰበካ ጉባኤ መምሪያ
6. ሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ
7. መንፈሳዊ ፍርድ ቤት
8. ሕግ አገልግሎት
9. የሕግ አማካሪ
10. አስተዳደር መምሪያ
11. ገንዘብና በጀት መምሪያ
12. ቁጥጥር አገልግሎት
13. የውጭ ጉዳይ መምሪያ
14. የቅርሳ ቅርስ ጉዳይ መምሪያ
15. ዕቅድና ልማት መምሪያ

ለ/ ኮሚሽንና በቦርድ የሚተዳደሩ፤

1. ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን
2. የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ
3. ቤቶችና ሕንፃዎች አስተዳደር

ሐ/ ድርጅቶች

4. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት
5. ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
6. አልባሳት ማዘጋጃና ምርት ስርጭት
7. የቁልቢ ቅ/ገብርኤል ገዳም ንዋየ ቅድሳት ማደራጃ
8. የጐፋ ጥበበ እድ ማሠልጠኛ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ

1. በቅዱስ ሲኖዶስ በሚሠየም አስመራጭ ክሚቴ አቅራቢነት ከሲኖዶስ አባላት መካከል ሦስት ዕጩዎች ተወዳድረው በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የተመረጠው ሊቀ ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ በቅዱስ ፓትርያርኩ ይሾማል።
2. ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት የተመረጠው ሥራ አስኪያጅ ሹመት ጉዳይ ለሚመለከታቸው ሁሉ በቅዱስ ፓትርያርክ ፊርማ ይገለጻል።
3. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስና ለቅዱስ ፓትርያርኩ ነው።
4. የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ነው አስፈላጊም ሆኖ ከተገኘ ለአንድ የምርጫ ዘመን እንደገና ሊመረጥ ይችላል።
5. ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሥራውን ለመቀጠል የማያስችል ምክንያት ካጋጠመው የአገልግሎቱ ዘመን ሳይፈጸም በቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ውሳኔ በሌላ ሊተካ ይችላል።

የጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

1. ቅዱስ ሲኖዶስ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በየጊዜው የሚወስናቸውን ጉዳዮችና ከቤተ ክርስቲያኒቱ ልዩ ልዩ መ/ቤቶችም ሆነ ከየሀገረ ስብከቱ የሚቀርቡትን ጥቃቄዎችን ሁለ በሕጉ መሠረት ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል።
2. የዋናውን መ/ቤት፣ ቦርዶችን፣ ኮሚሽኖችን፣ ድርጅቶችንና መምሪያዎችን እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ ሥር የሚገኙትን የሥራ ዘርፎች ሁሉ ያስተዳድራል፣ ይመራል።
3. ከቤተ ክርስቲያኒቱ አቅዋም ጋር የሚስማሙ ሥራዎችን በማካሔድና የገንዘብ ምንጭ በማስገኘት የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብርት የሚለማደትን ዘዴ እያጠናና በአስተዳደር ጉባኤ እያስወሰነ በሥራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ በቋሚ ሲኖዶስ በኩል ለቅዱስ ሲኖዶስ ያቀርባል ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል።
4. ማንኛውም የቤተ ክርስቲያኒቱ ገንዘብ በትክክል ገቢ መሆኑን በሕጋዊ መንገድ ወጭ እየሆነ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዋሉን ይቆጣጠራል።
5. የየዓመቱን የሥራ ፍሬና የወደፊቱንም ዕቅድ የሚያስረዳ ሪፖርት በየዓመቱ በጥቅምት ወር ለሚደረገው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ያቀርባል አጠቃላይ ጉባኤ የመከረበትና ያሳለፈው የውሳኔ ሐሳብ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ ሲጸድቅ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

ስለ ምክትል ሥራ አስኪያጅ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ምክትል ሥራ አስኪያጅ

- ከቅዱስ ሲኖዶስ በመመሪያ ተወስኖ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል።
- ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ በማይኖርበት ጊዜ ወክሎት ይሠራል። የሥራ ድርሻውም በውሰጠ ደንብ ተዘጋጅቶ በቋሚ ሲኖዶስ ጸድቆ ይሰጠዋል።
- ምክትል ሥራ አስኪያጁ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ይሆናል።

የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን

- ይህ ኮሚሽን የቤተ ክርስቲያንዋን ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦን በሚመለከት የተቋቋመ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድርጅት ነው።
- ኮሚሽኑ በቦርድ ይተዳደራል።
- ቦርዱ በቅዱስ ሲኖዶስ ይሰየማል፣ ተጠሪነቱም ለቅዱስ ሲኖዶስ ይሆናል።
- የኮሚሽኑ ኮሚሽነር በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርጦ በፓትርያርኩ ይሾማል።
- ኮሚሽኑ የሚመራው በቦርዱ ተዘጋጅቶና በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በመወጣ ደንብና መመሪያ ይሆናል፣ ተጠሪነቱም ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መብት

- ያሏትን ጥንታውያን መጻሕፍት እየተረጐመችና በማሳተሚያ ቤቶችዋ እያሳተመች ለተከታዮችዋ ምእመናን አገልግሎት ማዋል ትችላለች።
- ቤተ ክርስቲያኒቱ በአዋጅ ቁጥር 145/47፣ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ 299/57 አንቀጽ 4 እና 354/61 አንቀጽ 4 በሚያዝዘው ድንጋጌ ተጠቅማ ለጎብኚዎች ሥራዋ የሚያስፈልጉአትን ወረቀት፣ ቀለም፣ ኘሌት፣ ፊልምና የመሳሰሉትን ጥሬ ዕቃዎች፣ የምትገለገልባቸውን አልባሳትና ንዋያተ ቅድሳት ከውጭ አገር በርዳታና በግዥ ማስመጣት ትችላለች።
- የቤተ ክርስቲያን መገልገያ አልባሳት፣ መስቀል ጻሕል ጽዋና የመሳሰውትን ንዋያተ ቅድስት በራስዋ ሓላፊነት እየሠራችና እያዘጋጀች በአገልግሎት ላይ እንዲውል ታደርጋለች።
- ቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊትና ብሔራዊት እንደመሆንዋ ከጥንት ጀምሮ በሊቃውንት ልጆችዋ አማካይነት እየጻፈችና እያዘጋጀች ስትገለገልባቸው፣ ስትጠብቃቸውና ስታስተምራቸው የኖሩት በየገዳማቱ፣ በየአድባራቱና በየገጠር አብያተ ክርስቲያናቱ ያሏትን ልዩ ልዩ ቅርሶች ቤተ መዛግብት ሆና በጥንቃቄ ስትጠብቅ እንደኖረች ሁሉ አሁንም በያሉበት በባለቤትነት የመጠበቅና የማስጠበቅ መብት አላት።

- የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅርና አንድነቱን አጽንቶ የሀገሩን ዳር ድንበር ጠብቆ ነፃኑቱን አክብሮ የኖረው ከቀደምት አባቶቱ በወረሰው የግበረ ገብነት፣ የአገር ወዳድነት፣ የሃይማኖት ጽንዓት ስለሆነ የህንኑ ለትውልድ ለማስተላለፍ አስፈላጊ በሆነ ቦታ ሁሉ ትምህርት ትሰጣለች።
- ያቋቋመቻቸውን ማሠልጠኛዎችና ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤቶች በኮሌጅ ደረጃ ማሳደግና እንዲሁም አቅም በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ት/ቤቶችን ማቋቋም ትችላለች።
- ባቋቋመቻቸውን ት/ቤቶች ሃይማኖሪቷንና ቀኖናዋን ታስተምራለች፤ በየገዳማቱና እንዲሁም አቅም በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ት/ቤቶችን ማቋቋም ትችላለች።
- ንብረቷንና ይዞታዋን በሕግ ታስከብራለች።
- የሰንበት ትምህርት ቤቶችንና የበጐ አድራጉት ድርጅቶችን ታቋቁማለች።
- ሰንበታትንና ሌሎችንም ዐበይት በዓላት ታከብራለች ታስከብራለች።
- በአዲስ አበባና በየአህጉረ ስብከቱ ስብከተ ወንጌልን ታስፋፋለች።

የቤተ ክርስቲያን ግዴታ

- ቤተ ክርስቲያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረታት በምድር ያለች መንግሥተ እግዚአብሔር እንደመሆኗ መጠን ስለ ሀገርና ስለ ሰላም ትጸልያለች።
- ሕዝቦች በፍቅር፣ በሰላምና በአንድነት እንዲኖሩና ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲደርሱ በተለይም የድሆች ወገኖች ችግር እንዲቃለል ከበጎ አድራጊዎች ጋር በመተባበር ያልተቆጠበ ጥረት ታደርጋለች።
- በሰዎች መካከል የሚፈጠር የእርስ በእርስ አለመግባባትና ግጭት እንዲሁም በሕዝቦች መካከል ጦርነት እንዳይኖር የማስተማርና የማስታረቅ ሐላፊነት አለባት።

ሀ/ የሀገር ሰላም፣አንድነትና ዕድገት

ለ/ የወገን ነፃነትና ብልፅግና

ሐ/ የሰው ልጆች እኩልነትና ፍትሕ ርትዕ እንዲሰፍን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮዋን ታከናውናለች።

ስለ ቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ሀብትና ንብረት

- አንድ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበት ጊዜ የግል የሆነ ገንዘብ ቢኖረው ይረዳቸው ለነበሩ ዕዳለ ማውታና ችግሮች ይሰጣል። /አብጥሊስ 39/
- ኤጲስ ቆጶሱ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ሲያከናውንባቸው የቆዩት መጻሕፍት አልባሳት፣ አርዌብርት፣ መስቀሎች፣ መቋሚያዎችና የመሳሰሉት ሁሉ በቤተክርስቲያኒቱ ንብረትንት በስሙ ተመዝግበው በሀገረ ስብከቱ በሙዚየም ይቀመጣሉ።
- ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሊቀ ጳጳስ ወይም ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ፡

ሀ/ ሲታመም ከአቅሙ በላይ ከሆነ ቤተክርስቲያኒቱ ታሳክመዋልች፣

ለ/ ባረፈም ጊዜ ዜና ዕረፍቱ በመገናኛ ብዙኃን ይነገራል።

ሐ/ ሥርዓተ ቀብሩ በቅዱስ ፓትርያርኩና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ይፈጸማል።

መ/ በየሀገረ ስብከቱም ጸሎተ ፍትሐት ይደረግለታል።

ሠ/ ከዚህ በላይ ለተጠቀሰው ሁሉ የሚያስፈልገው የገንዘብ ወጪ ከሀገረ ስብከቱ ግምጃ ቤት ወጪ ይደረጋል። የሀገረ ስብከቱ የገንዘብ አቅም አማይችል መሆኑ ከተረጋገጡ አስፈላጊውን ገንዘብ ከጠቅላይ ቤተክህነት ግምጃ ቤት ወጪ እንዲሆን ጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ያዛል።